# ነፍጠኛ!




Local reports have said that in some places ethnic Oromo have attacked ethnic Amhara, and in Shashamane town some people were going home to home checking identity cards and targeting Amhara residents.




ስጋህን አድርገህ ጣራ አጥንትህም ወጋግራ፣
የአለት መሰረት አንጥፈህ የአገር አዳራሽ ብትሰራ፣
ዋው! ዋው! እያሉ ነከሱህ አብዶ እንደሚለክፍ ቡችላ፡፡

ደምህን እንደ ወንዝ አፍስሀ ድንበር ጠብቀህ ስለኖርክ፣
በደቆስካቸው ባእዳን የተንኮል አውታር ተጠልፈህ፣
በእነሱ አምላኪ ባንዳዎች በጥርስ በድድ ተነክሰህ፣
አንበሳው እንቅልፍ ሲይዝህ ጆፌዎች ኩስን ጣሉብህ!

ወርቁን በሰም ሸፍነህ ስለጋትክ የቅኔ ዘመራ ብርዝን፣
ቀለምን ጨምቀህ ተእጸዋት ቆዳውን ፍቀህ ብራናን፣
ተዓለማት በፊት ስለቻልክ ጥበብን መጣፍ ማንበብን፣
በቅናት ሰክረው ዶለቱ ሲያጠፉት ታሪክ ቅርስህን፡፡

ተፈጥሮን ዓይተህ ስዕሉን መጣፍ መርምረህ ጥበብን፣
ድንጋዩን ፈልጠህ ቤተክሲያን መሬት በርቅሰህ ጤፍ ምርትን፣
ስትመግብ በኖርክ ዓለምን ሌሎች ሲለቅሙ ዛፍ ፍሬን፣
ዝቅ ያለ መንፈስ ነዳቸው እንደ ገለባ አርጎ ብን፡፡

ጊዜን በቀመር ለክተህ ዓመቱን በወር ከፋፍለህ፣
የዘመን ስሌት አስልተህ የቀን ቆጠራን ስላተምክ፣
የራስ ወርቅ አያደምቅ ሆነና ላቲን ውሽማ ያዙብህ፡፡

ሰውን ተባድ አምልኮ ለዛፍ ተመስገድ ስላዳንክ፣
ተመስቀሉ ሥር ቁጭ እንዳልክ በተባ ስለት አረዱህ፡ ፡

ወራሪን ወገቡን ሰብረህ አገር ተክብሯ ባስረከብክ፣
ዘርህን ሊያጠፉ ዘመቱ ቀንደኛ ጠላት አርገውህ፡ ፡

አውሬዎች ስድብ መስኋቸው ሲጠሩህ አንተ ነፍጠኛ፣
ዝቅዝቅ ተመልከታቸው ከተራራው ላይ ውጣና፡ ፡

መቻልን እያንጎራጎርክ ፍሪዳ መሆን ተውና፣
ህልውናህን አረጋግጥ እንደ አያቶችህ አግሳና!

ይሶረፍብህ እምቢ በል ግፍ አንገት ደርሶ ሲፈላ፣
ዘርህን አድን ከመጥፋት ዘራፍ ነፍጠኛ በልና፡ ፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ሐምሌ ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.